# የሲቪክ ማህበራት ነገር በአደርባይነት ሲወራረድ

**ዮናስ 01/14/14**

የዚህ ጽሁፍ መነሻ ከ"ፋክት" ለ"ፋክት" ሲቪክ ማህበራትን በማስመልከት የቀረቡ ሁለት መጣጥፎች ናቸው። እነዚህ መጣጥፎች በአንድ ሳምንት ልዩነት በተከታታይና በተለያየ አጀንዳ ላይ የቀረቡ ናቸው። ፋክት1 ቁጥር 24 ታህሳስ 2006 በ"አሎሚልቀን ስናይ" ዓምድ በአምደኛው እንዳለ ጌታ ከበደ "ህዝባዊ አደርባይነት" በሚል ርዕስ የቀረበው በተሟላና ራሱን በቻለ ሁኔታ ሲቪክ ማህበራትን ባይመለከትም በአጀንዳው ከተነሱትና ለህዝባዊ አድርባይነት መገለጫ ሆነው ከቀረቡት ሶስት ነጥቦች ውስጥ የሲቪክ ማህበራት አካል የሆኑትን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተመለከተው በግልጽና በሁነኛ መንገድ የተተነተነ መሆኑ፣ በፋክት1 ቁጥር 26 ታህሳስ 2006 ፖለቲካ አምድ መስከረም አበራ በተባለች አምደኛ "የሲቪክ ማህበራትን ነገር ከአገራችን አንፃር"ከየሚለው የመስከረም መጣጥፍ እነሳለሁ።

አብዛኞቹን የፋክት መፅሂት አምደኞች የሚያመሳስላቸው ግን ደግሞ (ሆን ተብሎ (በተጠና መንገድ የሚሰሩት እንደሆነ የምገምተው) የሃሳቦቻቸው መዘወሪያ የፈረንጅ ጥናቶች መሆናቸው ነው። ስለሀገራችን ልማትና ዴሞክራታይዜሽን (አምነውም ሆነ ሳያምኑበት) እነዚህኑ ፈረንጅኛ ጽሁፎች በመጠቃቀስ ሊያሳምኑን መሞከራቸውም ሌላው የሚያመሳስላቸው ጉዳይ ነው። የአፃፃፍ ዘይቤያቸው ደግሞ አለሳልሰው በመጀመር ወይ ደግሞ ቀባብተው በመነሳት በአሉባልታ ማጠናቀቅ ነው።

በዚሁ መሰረት የሲቪክ ማህበራትን ነገር ከሀገራችን አንፃር ለመመልከት የሞከረችው መስከረም አበራ መነሻዋን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ለሲቪክ ማህበራት ወሳኝ ስለመሆኑና ማህበራቱም በተመሳሳይ ለሀገር ብልፅግና ወሳኝ ስለመሆናቸው በማውሳትና ግን አምባገነን መንግስታት እነዚህን ማህበራት ለራሳቸው ፖለቲካዊ ፍጆታ ካልሆነ በስተቀር እንደማይሿቸው በመግለፅ ነው።

ከመስከረም ጋር በዚህ ነጥብ ጠብ የለኝም። የነገስታቱንም ሆነ የደርጉን ስርዓት ስለጥላቻ ፖለቲካ ስትል በመጠኑ ገጭታ አሁን ያለውን ስርዓትም ከእነርሱ እንደሚሻል አውስታ ስታበቃ የ"መሻል" ያለችውን ወደ የ"ባሰ" ዘመን በሚል ቀይራ ሃሳቧን መቋጨቷ ነው።

ስለሆነም ከገዛ ሃሳቧ ጋር ያደረገችውን መዛነፍ ለአንባብያን ትተን ከዚያ ባሻገር ያለውን ትርክቷን ከወቅቱ የሲቪክ ማህበራት ሁኔታና ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ተመልክተን ሂሳብ ልናወራርድ ግድ ይለናል።

"ለሀገራችን የዴሞክራሲን ጭላንጭል በማሳየቱ ረገድ ኢህአዴግ ከቀደምቶቹ የተሻለ ነው" ብላ በመሻሉ ዘመን ርዕሰ ጉዳይዋ ላይ ያነሳችው መስከረም ለዚህ ምስክርነትዋም የማህበራዊ ጥናት መድረክን (ማጥማ) የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበርን፣ አክሽን ኤይድ ኢትዮጵያን፣ ኢንተር አፍሪካ ግሩፕን፣ ኢሰመጉን እና የመሳሰሉትን ህዝቡ መብቱን አውቆ እንዲያስከብር ግንዛቤ በማስጨበጥና የብዙሃኑን የፖለቲካ ንቃት ከፍ ከማድረግ አኳያ ሚናቸው ከፍተኛ ነበር ስትል በአስረጅነት አቅርባለች።

ከዚያም ከመሻል ወደመባስ ለሚለው ትርክቷ ስታመራ የ2000 ውን የሲቪክ ማህበራት ህግ በዋናነት ታነሳለች። ከዚህና የሲቪክ ማህበራትን ከተመለከተው ህግ በተለይ በጀትን የተመለከተውና ዴሞክራታይዜሽን ላይ ለሚሰሩ ሲቪክ ማህበራት የገቢ ምንጫቸው 90 በመቶ ከሀገር ውስጥ እንደሆነ የሚደነግገውን ነጥብ “የመለስ ዜናዊ የአምባገነንት ፖለቲካዊ ትሩፋት ነው” ስትል ለሰጠችው ድምዳሜ ሞኒተር የተባለ ድረገፅ ፌብሪዋሪ 28/2013(Ethiopia makes help difficult for world donors advocating civil socity rights በሚል ርዕስ ማስነበቡን ዋቢ አድርጋለች፣ (ይህ ዋቢዋን ደግሞ በመግቢያዬ አካባቢ ከጠቀምኩት የመጽሄቷ አምደኞች የአፃፃፍ ዘይቤ አኳያ አንባቢያን እንዲጠይቁ እሻለሁ።)

በዚህ የማታበቃው መስከረም "መብትን ሳያውቁ ልማት?" በሚል ላነሳችው ጥያቄም አርሶ አደሩ መንደር ዘልቃ አጓጉል ፖለቲካ ፈትፍታለች። መቋጫዋም ያው በተለመደውና ቀደም ብሎ በተመለከተው መንገድ “በሀገራችን የዜጎች መብት ላይ የሚሰሩ የሲቪክ ማህበራት የህጋዊነት ሽፋን በተሰጠው አፋኝ አዋጅ ከጨዋታ ውጭ በመደረጋቸው ስለዜጎች መብት መማማር፣ ግንዛቤ መፍጠርና መከራከር አልተቻለም” የሚል ሆኗል።

ለዚህና በጥቅሉ ለቀረበው የመስከረም የሲቪክ ማህበራት ትንታኔ መጀመሪያ በእንዳለ ጌታ ቀርቦ ከነበረው እና ከእርሷ መጣጥፍም አስቀድሞ ለንባብ ከበቃው "ህዝባዊ አድርባይነትን" ከተመለከተው መጣጥፍ ማወራረጃ የሆነውን ሃሳብ አንስቼ ወደተጨባጩ የሲቪክ ማህበራት ጉዳይ አመራለሁ። እንዳለ ጌታ "ህዝባዊ አድርባይነት" ሲል በሰየመው መጣጥፉ ያነሳቸው ሃሳቦች ላይ (መንግስታዊ አድርባይነትን፣ ህዝባዊ አድርባይነትን እና ምዕራባዊ አድርባይነትን የተመለከቱ) ብስማማም ለዚህ ትርክ ማወራረጃ ሆኖ ከተገኘው ምዕራባዊ አድርባይነት ስር የተገለፁ ሃሳቦችን ብቻ ለማንሳት እገደዳለሁ።

"--ምዕራባዊ አድርባይነት ደግሞ አለ - ሌላ ስም አጥቼለት እንጂ ምዕራባዊነት ስል በመንግስት ስር ያልሆኑ፣ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ ግለሰቦች እና ተቋማት የሚመሩ አካል ማለቴ ነው፣ እዚህ ተቀጥረው ለአለቆቻቸው መረማመጃ ለመሆን ራሳቸውን አንጥፈው የሚሸጡ፤ <u>ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን አገራቸውን የሚሸጡትን</u> መጥቀሴ ነው። ስለነዚህ አደርባዮች ቡዙውን ጊዜ ሲነገር አልሰማም፣ እንዲህ አይነቱ አደርባይ ስንሆን <u>እስከተከፈለን ዩሮ እና ዶላርን እስከመነዘርን ድረስ ለተረፈውና ለተቀረው ጉዳይ ግድ የለንም</u>፣ አንዳንድ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስራቸው ይኼ ነው፣ በውድ ዋጋ ይገዙናል፣ የከበረ ወንበር ያሰናዱልናል፣ በየባህር ማዶው ያስደሶክሩናል ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን ራሳችንን እና አገራችንን ሙክ ብለን ስንሰድብ ነው። "ፈረንጅ ባይደርስልን ኖሮ ተናንቀን እንተላለቅ ነበር" ስንል ነው፣ "ፈረንጅ ባይደርስልን ኖሮ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተተብትበን እንሰቃይ ነበር" ስንል ነው። ቀፋፊ እና አስነዋሪ ስድቦችን ተሳድበን፣ ህዝባችንን በፈረንጅ አፍ ከስሰን፣ አቂማዳችንን ሞልተን፣ ደስ በሚያሰኛቸው መንገድ ጥናታችንን አገባደን፣ ህይወቴም መንገዴም ፈረንጅ ነው ብለን፣ ወደ ሀገራችን ስንመለስ ነው አድርባይነት፣" (ሰረዝ የእኔ)።

የከበረ ወንበር ተሰናድቶለት በውድ ዋጋ የተገዛና ፈረንጆቹ ደስ በሚላቸው መንገድ ጥናት ሲሰራ የኖረው ማነው? የሚል ጥያቄ ለመስከረም አነሳለሁ። በምርጫ ታዛቢነት መታወቂያ ሀገሩን ሙክ ብሎ ሲሰድብ የነበረውና በፈረንጅ አፍ ሲከስ የነበረውንም ማነው? ፈረንጅ ባይደርስልን ኖሮ፤ (እና ጎሜዝና ቲምክለርከን ባያድለን ኖሮ) ተላልቀነው ነበር ብሎ በአደባባይና በፈረንጅ ሚዲያ ሲደሰኩር የነበረው ማነው? ብዬ መስከረምን ጠይቃለሁ።። መቼም መልሱ ለገዢ ስርዓቱ ካለፉት መንግስታት የተሻለ መሆንነት እንደማሳያ በመስከረም በኩል የተጠቀሱት ማህበራትና አመራሮቻቸው የነበሩ ስለመሆናቸው እርሷም

የምትክደው አይመስለኝም። ስለሆነም መስከረም የሲቪክ ማህበራትን ነገር ከአገራችን አንፃር ብላ ላነሳችው ሃሳብ ትክክለኛው መልስና  በልክ የተሰፋው ነጥብ የበጎ አድራጎትን የተመለከተው አዋጅ አይመስለኝም። ይልቁንስ አዋጁን በተመለከተ  በመስከረም በኩል የሰፈሩት ነጥቦችም ሆኑ ማንፀሪያዎች ተዛንፎ የተቆለፈ ሽሚዝ አይነት ነው የሆኑብኝ። ስለሆነም ደግሞ ለዚህም በመስከረም በኩል ለተነሳው አጀንዳ ሁነኛ የሆነው መደምደሚያ "ምዕራባዊ አድርባይነት" የሚለው ይመስለኛል። ምክንያቱ ደግሞ ከላይ ላነሳኋቸው ጥያቄዎች ቀድሞም መልስ የነበሩት ተቋማቶችና አመራሮቻቸው በተለይም መስከረም ለማንሳት የሻቻቸው 97 ምርጫ አካባቢ የነበሩ አመራሮቻቸው ዛሬም ከምዕራባዊ አድርባይነታቸው ያልተላቀቁና ለዩሮና ለዶላር ተገዝተው በፈረንጅ አፍ ህዝባቸውን እየከሰሱና አገራቸውንም ጭክ ብለው እየተሳደቡ መሆናቸው ነው።

አሁን ደግሞ የምዕራባዊ አድርባይነትን ትርክት ወደሚደግፉልኝ  አስረጅዎች በአንድ በኩል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለመስከረም የተሳሳተ ድምዳሜ ማጋለጫ ወደሚሆኑልኝ ነጥቦች አመራለሁ።

የሲቪክ ማህበራት ፅንሰ ሃሳብ ሰፊና ጥልቅ ቢሆንም ከመስከረም አንፃር የቀረበልንን ብቻ ለመፈተሽ የሲቪክ ማህበራት አውራ የሆነውን ተቋም ማንሳት በራሱ በቂና ሌላውንም ማሳያ ይሆነናል። ተቋሙ ሂዩማን ራይትስ ዎች የተባለውና የሰብአዊ መብት ተሟጋች ነኝ የሚለው ግዙፍ ተቋም ሲሆን ይህን ተቋም እንደማሳያነት ለመውሰድ የፈቀድኩበትም ተጨማሪ ምክንያት አለኝ። ይኸውም እንደጥሩ የሲቪክ ማህበር ተቆጥረው በመስከረም በኩል ከተወደሱት መካከል አክሽን ኤይድ የተሰኘው ይገኝበታል። ታዲያ የዚህ ተቋም የፖሊሲ ዲፓርትመንት ሃላፊ የነበሩትና ስራቸውም በህግና በነፃነት መሆኑን ሲነግሩን የነበሩት አቶ ዳንኤል በቀለ በተቋሙ ስም የገቡባቸውን የፖለቲካ ጓዳ ጎድጓዳዎች ሳንዘነጋ አሁንም ለዚያ ውለታቸው፣ ለዚያ ጭክ ያለ ስድባቸው በሽልማት በቀረበላቸው የሂዩማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ዳይሬክተርነት የተደላደለ ወንበራቸው ላይ ቁጭ ብለው አደርባይነታቸውን መቀጠላቸው ነው።

ስለሆነም አቶ ዳንኤል ይመሩት የነበረው ተቋም የሂዩማን ራይትስ ዎች ግልበጭ መሆኑን በዚህ ብቻ ካረጋገጥን ዘንድ ይህ ተቋም አሁን ያለበትን ደረጃና ተቋማዊ ቁመና ስንመለከት የሲቪክ ማህበራትን ነገር እና የሀገራችንን ሁኔታ መስከረም ካነሳችው የመከራከሪያ ሃሳብ በተቃራኒው ላይ ሆኖ እናገኘዋለን። በሰብአዊ መብት ጥበቃና አያያዝ

ጉዳዮች ላይ ንቃተ ህሊና የሚፈጥሩ ስትል መስከረም ያወደሰቻቸውን እና "በአፋኙ አዋጅ" ከጫወታ ውጪ ሆነዋል ከምትላቸውን ተቋማት መቼም ስለሰብአዊ መብት ከተባለ ረጂና መሪ ሆኖ የሚመጣውና የሚታየው ሂዩማን ራይትስ ዎች ነው።

ታዲያ ይህ ድርጅት በስራ ላይ በቆየባቸው 34 ያህል ዓመታት ከገነባው አለም አቀፋዊ ስምና አቅም በላይ በሚገርሙና ግራ በሚያጋቡ ወቀሳዎች የተከበበ ነው። ሲብስም የተቋሙን አለም አቀፋዊ አቅም የተገነዘቡ በርካቶች በተለይ ምዕራባዊ አደርባዮች "የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ልዕለ ሃያል" ሲሉት ይደመጣል። የሚሰነዘሩበት ወቀሳዎች ይዘትና አይነት ግን ከዚህ አቅሙ ጋር የማይመጣጠኑ “የማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ” አይነት የመሆናቸው እውነት በተቋሙ ዙሪያ አያሌ ጥያቄዎች እንዲነሱ አድርጓል። እያደረገም ነው፣ ወደፊትም እንደሚቀጥል እርግጥ ይመስላል። በሰብአዊ መብት ጥላ ስር ፖለቲካዊ አጀንዳዎችን ማራመድ፣ደረጃቸውን ያልጠበቁና ኢ-ስነምግባራዊ “ጥናቶች” ማሰራጨት፣ ሉዓላዊነትን የሚጥሱ፣ በወገንተኝነት የሚመሩ ጣልቃ ገብነቶች በማድረግ፣ፖለቲካዊ ተቃውሞዎችን በማገዝና በማስተባበር፣የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን አጋኖና አዛብቶ ማቅረብ፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲሰፍን በሚል ሽፋን የመንግስታትን ስልጣን መሻማትና ሀገራዊ ሰላምን ማደፍረስ፣ ግለሰባዊ የፖለቲካ አቋሞችን ማራመድ፣ሀገራትን በአድልኦ በመመልከት፣ምንጫቸው ያልተጣሩ የገንዘብ ምንጮችን መጠቀም ወዘተ - - - ወንጀሎች በየአደባባዩ ይከሰሳል።

በእሥራኤልና ፍልስጤም ጉዳይ፣ የጆርጂያና ዩክሬን አመፃች፣ የሰሜን አፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ የእርስ በርስ ግጭቶችና አመጾች፣ የምርጫ 97 በኢትዮጵያ ግርግሮችና የቀለም አብዮት ሙከራዎች፣ የኬንያ የምርጫ ሂደት ግርግር፣በመሬት ወረራና የሃይማኖት ነፃነት ስም ኢትዮጵያ ላይ የወጡ ሪፖርቶች፣ ወዘተ የተቋሙ ከላይ የተመለከቱ ወቀሳዎች ሁነኛ ማሳያዎች ሲሆኑ እነዚህም የተሰሩትና የሚሰሩት በተቋሙ ብቻ ሳይሆን መስከረም ባለቻቸውና ከጨዋታ ወጡ ስትል በተቀረቀረችላቸው ምዕራባውያን አደርባዮች ነው።

ታዲያ ይህ ተቋም በየጊዜው በየሚዲያው ከሚያወጣቸው የሰብአዊ መብት ጥሰቶችና ተዛማጅ ጉዳዮች ሪፖርቶች እኩል እጅግ በጣም ብዙ ሀገራት ከቀላል እስከ ተደራጀ መልስ ሰጥተውታል፣ እየሰጡትም ነው። ይህ ደግሞ መስከረም እንዳለችው በጭፍንና በብልጣብልጥነት ሳይሆን በርካታ የተቋሙን ኢ ፍትሃዊነት የሚያሳዩና በየሀገራቱ የተሰሩ

ጥናቶችን መሰረት በማድረግ ነው። በነገራችን ላይ የተቋሙ የማይፈለግ ጣልቃ ገብነት የበዛባቸውና ሉዓላዊነታቸው የተደፈረባቸው ሀገራት ይህን ተቋም ለመቃወም ሲሉ ልዩ ግብረ ሃይል ማቋቋማቸው በአለማችን ያለ እውነታ መሆኑ አፅንኦት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ይመስለኛል።

ሀገራችንም በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ በተለያዩና በማይመለከተው ይልቁንም ከሰብአዊ መብት ጋር በማይገናኙ ጉዳዮች ላይ ሁሉ የዚህ ተቋም ሰለባ ሆና እንደቀጠለች ነው። ስለሆነም እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎች ያሉ ድብቅ ፖለቲከኞችና፣ የጥላቻ ፖለቲካ አራማጆች ለየትኛውም ሀገር ስጋት የመሆን አቅማቸው ከፍተኛ ነው። በተለይም የሚሰማቸው ህዝብ ካገኙና በርከት ያሉ አደርባዮች ካገኟቸው የፖለቲካ ስርዓቱን እስከማናጋት ይደርሳሉ፤ የሀገርን ቅኝት ያዛባሉ። ለዚህና በሲቪክ ማህበራት ስም የሚንቀሳቀሱ ሃይሎችን አደገኛነት ለተመለከተው ነጥብ ጥሩ ማሳያ ከምርጫ 97 ላይ ጠቅሰን የነገረ አደርባይነትን እና የሲቪክ ማህበራን ጉዳይ እናጠቃል።

ጉዳዩን ያስነበበን አቶ ዳንኤል የተባለ ብሎገር/ ጦማሪ ነው። "ሂዩማን ራይትስ ዎች ህዝቡ ለምርጫ እንዲመዘገብና እንዲመርጥ “ይደረግበት የነበረውን ግፊት” በሪፖርት ሲገልጽ እንዲህ በሚል መንገድ ነበር። “ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግን አልመርጥም የሚል ህዝብ እንዳይበዛ በመስጋቱ በሚያዝያ እና በግንቦት ውስጥ ባለሥልጣናትና ሚሊሻዎችን (ታጣቂ የሚባሉትን) ቤት ለቤት በማሰማራት እንዲመዘገብና ገዢውን ፓርቲ እንዲመርጥ ሲያደርግ ነበር” አቶ ዳንኤል በዚህ መልኩ የድርጅቱን ሪፖርት በአጭሩ ከገለፁ በኋላ የሚከተሉትን ሶስት ጥያቄዎችን ያነሳሉ።

በሚያዚያና ግንቦት የመራጮች ምዝገባ ነበርን? በአዲስ አበባ ኸረ እንዲያውም በሌሎች የኢትዮጲያ ከተሞችስ ሚሊሻ የሚባል ነገር አለን? ከአዲስ አበባ ነዋሪዎች መካከል ፖሊስን በስህተት እንኳን ታጣቂ ወይም ሚሊሻ ሲል የሚጠራ አንድ ሰው ይገኝ ይሆን?

የአቶ ዳንኤል ብርሃኔ መልስ አዘል ጥያቄዎች ለአለም የሚያስተላልፉት ከባድ መልዕክት ይዘዋል። ሂዩማን ራይትስ ዎች “ትዝብቴ” “በምርምር ያረጋገጥኳቸው” “በጥልቅ ጥናቴ ያገኘዋቸው” ወዘተ....እያለ ለአለማችን ግዙፍ ሚዲያዎች የሚያቀርባቸውን ዘገባዎች

“የምዕራባውያን አደርባዮች” ውጤቶች ስለመሆናቸው እንድናረጋገጥ ያደርጉናል። "የምርምሮቻቸው" ብቃት በዶላርና ዩሮ የተመዘኑ መሆናቸውንም ምልከታ ይሰጡናል። በርካታ ሀገራት ለበርካታ ጊዜያት ለሰነዘሯቸው ወቀሳዎችም የማይናቅ እውቅና እንድንሰጥ ያስገድዱናል።ስለሆነም የሲቪክ ማህበራት ነገር ከሃገራችን አንጻር የሚመስለው ይህንኑ ነው።